# ቱለረሚያ (Tularemia)

ቱለረሚያ በባክተሪያ የሚመጣ በሽታ ሲሆን በሰውነት እነደአገባቡ ዓይነት የተለያዩ ምልክቶች ሊያሳይ ይችላል። በሽታውን የሚያመጣው ህዋስ በአካባቢያችን በዱር አራዊትና በአንትሮፖዶች (ለምሳሌ በአሜሪካ በመዥገርና በሚዳቋ ዝንብ፤ በሌሎች አገሮች ደግሞ በትንኝ) ይመጣል። ቱለረሚያ በቨርጂኒያ እምብዛም አይገኝም።

## ቱለረሚያ ማንን ይይዛል?

ቱለረሚያ ማንንም ሊይዝ ይችላል። ሆኖም በአብዛኛው የሚያጋጥመው በአዋቂዎች በክረምት ወራት አይጦችን ለማደን ሲወጡ ሲሆን በህፃናት ደግሞ ዝንብና መዥገር በሚበዛበት በበጋ ወራት ነው። በርከት ያሉ ሰዎች በቱለረሚያ መያዛቸው ከታወቀ የበሽታውን መንስኤ ለማጣራት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ምርመራ ያደርጋል።

## ቱለረሚያ እንዴት ይተላለፋል?

ቱለረሚያ ከሰው ወደ ሰው በቀጥታ አይተላለፍ እንጂ በሽታው በተለያዩ መንገዶች ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ የአዳኞች ቆዳ፣ ዓይን፣ አፍና ጉሮሮ የዱር አራዊቶችን በተለይ ጥንቸልና መሰል እንስሳት ቆዳ በሚገፉበትና የእነዚህን አራዊት ቆዳ በሚለብሱበት ጊዜ ለባክቴሪያው ሊጋለጡ ይችላሉ። በባክቴሪያው የተለከፉ እንሰሳት ሥጋ አያያዝና አሠራር፣ የእንስሳት ቆዳና የእግር ጥፍር አዘገጃጀት፣ የተበከለ ውሃ መጠጣት ወይም በበሽታው በተለከፉ የተወሰኑ የአንትሮፖድ እንስሳት መነደፍ (መነከስ) በሽታውን ሊያስተላልፍ ይችላል። ሌላኛውና እምብዛም የማያጋጥመው መንገድ ቢኖር ከተበከለ አፈር የተነሳ አቧራ መሰል ጋዛማ ዝቃጮችን ከአየር ጋር በማስገባትና ድርቆሽ ወይም እህል ከመሳሰሉት ነው።

## ቱለረሚያ ለባዮግብረ ሽበራ ተግበር መጠቀም ይቻላልን?

አዎን። ቱለረሚያ ለባዮግብረ ሽበራ ተግባር መጠቀም ከሚቻሉ ነገሮች ውሰዋ አንዱ ነው። ምክንያቱም ቱለረሚያ በጣም ተላላፊ ከመሆኑም በላይ በቀላሉ ማሰራጨትም ይቻላል። በበሽታው ብዙ ሰው በጣም ሊታመም ወይም ሊሞት ይችላል። በባዮ ግብረ ሽበራ ተግባር ቱለረሚያ የሚለቀቀው በአብዛኛው በተረጨ ዝቃጭ መለክ ሊሆን ይችላል።

## የቱለረሚያ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

የቱለረሚያ አያያዝ መንገዶች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን በዚያው ልክ የቱለረሚያ በሽታ አይነትም የተለያየ ሊሆን ይችላል። እነዚህም የቆዳ አልሰር፣ በጣም የሚያሳምም የአካል ውሰዋ በጉሮሮ የሚገኙ ዕጢዎች ሕመምና እብጠት፣ የዓይን ቅላት የጉሮሮ መከርከር፣ የአፍ አልሰርና ኒሞኒያ ዓይነት በሽታዎች ናቸው። በቱለረሚያ በሽታ እንደተጠቁ የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት የራስ ምታት፣ የጅማት ሕመም፣ የመገጣጠሚያዎች ሕመም፣ ደረቅ ሳልና እየተዳከሙ መሄድ ዋና ዋና ምልክቶቹ ናቸው። ኒሞኒያ በነዚህ ሁሉም ዓይነቶች ተወሳስቦ የሚፈጠር ሊሆን ከሞት ለመትረፍ ወዲያውኑ ምርመራና ተገቢውን ሕክምና ማድረግ ያስፈልጋል።

## የበሽታው ምልክቶች የሚታዩት በበሽታው ከተጋለጡ ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው ?

ምልክቶቹ ለበሽታው ከተጋለጡ ከ3 እስከ 14 ባሉት ማናቸውም ቀናት ሊታዩ ይችላሉ። በአብዛኛው ግን ለበሽታው ከተጋለጡ 3 ሦስት እስከ 5 ባሉት ቀናት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ መልክቶች ይታያሉ።

## በምርመራ እንዴት ይታወቃል እንዴትስ መታከም ይቻላል?

ቱለረሚያ የሚታወቀው በላቦራቶሪ ልዩ ምርመራ ነው። እንደቱለረሚያው ዓይነት ናሙናዎች ከሰውነት ከተለያዩ ቦታዎች ሊወሰዱ ይችላሉ። በጊዜው ፀረ ባክተሪያ (አንቲ ባዮቲክ) መድሃኒት መውሰድ ያስፈልጋል። በተፈጥሮ በሚተላለፈው ቱለረሚያ ምክንያት ሞት ብዙም አያጋጥምም። ቱለረሚያ በጣም አደገኛ የሚሆነው በአየር መልክ ወደ ወስጥ ሲገባ ነው።

## ቱለረሚያን እንዴት መከላከል የቻላል?

1. በአንትሮፖድ እንስሳት መነደፍን (መነከስን) ይከላከሉ። ነፍሳት በሚበዙባቸው ቦታዎች ከሆኑ ነፍሳቱን መከላከል የሚያስችሉ አልባሳት ይልበሱ።
2. በዱር እንሰሳት ከተነከሱና እንስሳው በበሽታው መበከሉ ከታወቀው ውሃ አይጠጡ፣ አይታጠቡ፣ አይዋኙ ወይም አይስሩ።
3. ቆዳ በሚገፉበት ጊዜ በተለይም የጥንቸል ከሆነ ጓንት መጠቀምን አይርሱ።
4. የጫካ ጥንቸሎችን አይጦችንንና አይጠ መጎጦችን በሚመገቡበት ጊዜ በደንብ ይቀቅሉት።
5. ሕፃናት ልጆች የጫካ (የበረሃ) ጥንቸሎችንና ሌሎች በቱለረሚያ ሊበከሉ የሚችሉ እንስሳትን እንዳይነኩ ከነኩም አስፈላጊውን ጥነቃቄ እንዲያደርጉ ይመከሩዋቸው።
6. ቱለረሚያን በተመለከተ በላቦራቶሪ የሚሠሩ ከሆነ ተገቢውን መከላከያ ዕቃዎች ይጠቀሙ። በተገቢው ማስቀመጫም ያስቀምጡት።

የቱለረሚያ ክትባት በአሁኑ ጊዜ በምግብና መድሃኒት አስተዳደር እየተሞከረ ያለ ሲሆን፣ በቱለረሚያ መጋለጥዎን ከተጠራጠሩ ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያ በመሄድ አስፈላጊውን የሕክምና ምርመራ ያድርጉ።

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH
Protecting You and Your Environment
www.vdh.state.va.us

እ.ኤ.አ. ሚያዚያ 30 2003 እንደተሻሻለው
AMHARIC: Tularemia Fact Sheet